ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

Coalition for Unity and Democracy Party
(Kinijit)

Date - Augus 1, 2006
No. KIL_PR_AMH004

"ኤሎሄ! ኤሎሄ!"

# በሊባኖስ በርሃ የሚፈሰውን የኢትዮጵያዊያን ዕንባ እናብስ!

ኢትዮጵያዊያን ከምንግዜውም በላይ አገራቸውን እየለቀቁ በስደት የሚኖሩበት አሳዛኝ የታሪክ ምእራፍ ላይ መሆናችን የሚያሳዝነንን ያህል፣ በስደት ሲንገላቱ ማየት ደግሞ ይበልጥ ልባችንን ያደማዋል። በሃገራችን የተንሰራፋውን ስራ አጥነትና ብልሹ የሆነውን የመለስ ዜናዊ አስተዳደር በመሸሽ ወገኖቻችን በመላው አለም ላይ ቢገኙም፣ ሁሉም በያለበት የስቃይ ሰለባ ቢሆንም፣ በሊባኖስ የሚገኙ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ጩኸት ግን ገደቡን አልፎ ከዳር እስከ ዳር እያስተጋባ ነው።

በአሁኑ ወቅት በመካከለኛው ምስራቅ በተነሳው የጦርነት እሳት ኢትዮጵያዊያን እየተማገዱ ናቸው። ከዚህ የተረፉትና በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩትም በአንድነት ተሰብስበው በፀሎትና በለቅሶ ኤሎሂያቸውን በማሰማት ላይ ይገኛሉ። "የድረሱልን" ጩኸታቸውም ከምጊዜውም በላይ አይሏል። በደህናው ጊዜ የመሰረቱት ቤተ ክርስቲያንና መስጊድ መሸሸጊያቸው አልሆኑም። ቤታቸውንና ከተማቸውን ለቀው በበርሃ ላይ የቀሩ፣ የሞታችውንም ቀን በመቁጠር ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ብዙ ናቸው። በስፍራው የሚገኘው የመለስ ዜናዊ አስተዳደር የሚመራው ኢምባሲም የራሱን ሰዎች ከማሸሽ አልፎ ለብዙሃኑ ኢትዮጵያዊያን አንዳች ቁምነገር አልፈየደም። ይልቁንም አጋጣሚውን ምክንያት በማድረግ በሞትና በህይወት መካከል ከሚገኙት ዜጎቻችን ገንዘብ በመሰብሰብ ርካሽ ተግባር በመፈጸም ላይ ነው። ለዚህም የመለስ ዜናዊ አስተዳደር በታሪክና በህግ ምንጊዜም ቢሆን ከተጠያቂነት አይድንም።

ትላንት በጀልባና በእግራቸው ባህርና በርሃ ያቋረጡት ኢትዮጵያዊያን፣ ዛሬም ከፊታቸው ሌላ ባህርና ሌላ በርሃ ተደቅኖባቸዋል። ከመካከለኛው ምስራቅ የእሳት ወላፈን ለመሸሽ ወደ ሶርያና ወደ ሌሎች አገሮች ቢሰደዱም ህይወታቸውን ለማቆየት የሚችሉበት ሁኔታ ግን እየተመናመነ መጥቷል። በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ለቅሶ ከሊባኖስና ከሶሪያ በርሃ አልፎ በአገር ቤትና በሌሎች አገሮችም እየተስተጋባ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት ወላጆቻቸውም በልጆቻቸው ሁኔታ፣ ፊታቸው በእንባ እየታጠበ የሚያደርጉት ጠፍቷቸው ሌትና ቀን በጭንቀት ላይ ይገኛሉ።

ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የነዚህ ወገኖቻችንን ጩኸት ለማስተጋባት የተባበሩት መንግስታትና የቀይ መስቀል ጽ/ቤቶችን በማነጋገር አስፈላጊው እርዳታ እንዲደረግላቸው ጥረት ሲያደርግ ነበር፣ አሁንም በማድረግ ላይ ነው። ሆኖም ይህ ጥረት በአንድ ድርጅት ብቻ ተከናውኖ፣ አስፈላጊው ውጤት በፍጥነት ሊገኝ አይችልም። በመሆኑም በመካከለኛ ምስራቅ ለሚገኙት ወገኖቻችን ከእንባ ይልቅ እርዳታችን ያሻቸዋል፣ ከለቅሶ ይልቅ ጩኸታቸውን ማስተጋባት ይጠበቅብናል። ይህም ዛሬ ልናደርጋቸው ከሚገቡን በርካታ ተግባራት አንደኛው ሆኗል። ስለሆነም... በመላው አለም የምትገኙ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ አባላትም ከሌላው የህብረተሰቡ ክፍል ጋር በመሆን፣ በፍጹም ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የተባበሩት መንግስታትና የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል አስፈላጊውን እርዳታ እንዲያደርግ ትማፀኑ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በአገራችን ያለውን ስራ አጥነትና ብልሹ አስተዳደር በመሸሽ፣ ቤተሰባቸውን ለመጦር በርሃ አቋርጠው ከወጡ በኋላ ዛሬም በርሃ ላይ ለወደቁት ወገኖቻችን እንድረስላቸው። ኤሎሂያቸውንም በማስተጋባት ጩኸታቸውን ለመላው አለም እናሰማላቸው።

የቅንጅት አለም አቀፍ የህዝብ ግንኙነት ክፍል።